# የፓስተር ዳንኤል ጭብጥ የሳተ ምስክርነት

* በዳዊት ከበደ

የዛሬ ሁለት አመት፤ በዕለተ ፋሲካ ጠዋት እጄ ላይ የነበረው ሞባይል አንቃጨለ:: ቀደም ብዬ የማውቀው ቁጥር ነበርና «እንኳን አብሮ አደረሰን» የሚል የአክብሮት ምላሽ ሰጥቼ የተለመደውን በቀልድ የታጀበ ሰላምታ ተለዋወጥን:: ደዋይዋ ወ/ሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ ነበረች:: በወቅቱ በእስር ላይ የነበረውን አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) በጋራ ሄደን እንድንጠይቀው ከቀናት በፊት ሀሳብ አቅርባልኝ ነበርና «ተዘጋጅተሃል ወይ» ለማለት ነው አደዋወሏ:: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ተገናኝተን ጉዞ ጀመርን:: ብርቱካን እግረመንገዷ ቦሌ መንገድ ከፍላሚንጎ ሬስቶራንት አለፍ ብሎ ከሚገኘው «ካሊፎርኒያ ፍላወር» ለአመት በዓል ስጦታ የሚሆን ማራኪ አበባ ገዛችና ቃሊቲ ደረስን:: በማረሚያ ቤቱ በር ላይ የነበሩ የጥበቃ ባልደረቦች ግን «የስጋ ዘመድ አይደላችሁም» በማለት ሊያስገቡን ፍቃደኛ አልሆኑም:: የሕግ ባለሙያዋ ብርቱካን በጥበቃ ስር ያሉ እስረኞች የመጎብኘት ሕገ መንግስታዊ መብት እንዳላቸው ሕገ መንግስቱን እየጠቀሰች ለማስረዳት ሞከረች:: አንዴ «አይቻልም» ተብሏልና ያዘጋጀችውን ስጦታ እቦታው ላይ ለነበሩ የአርቲስቱ ዘመዶች አስረክባ አብረን ተመለስን::

ይህ የዛሬ ሁለት አመት በዕለተ ፋሲካ የሆነው ነው:: በዘንድሮ ፋሲካ ግን ብርቱካን በተራዋ በዚሁ እስር ቤት ትገኛለች:: ቴዲ ደግሞ ተፈቷል:: ብርቱካን ከ2 ዓመት በፊት በማረሚያ ቤቱ በር ላይ ያቀረበችውን ሕገ መንግስታዊ መከራከሪያ በመንተራስ «ገብተን እንጠይቅ» ለሚሉ ሰዎች ዛሬም ምላሹ ተመሣሣይ ነው «የስጋ ዘመድ አይደላችሁም» የሚል::

ይህን ፅሁፍ ለማቅረብ መነሻ የሆነኝ ባለፈው ሰኞ በማረሚያ ቤት የሚገኙ እስረኞች አያያዝ አስመልክቶ ኢቴቪ ያቀረበው ዝግጅት ነው:: አለም አቀፉ የሰብአዊ መብት ተከራካሪ ድርጅት «ሂዩማን ራይትስ ዎች» የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት አመታዊ ሪፖርት የብርቱካን የጤና ሁኔታ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ነው የሚል መግለጫ ይፋ ባደረጉ ማግስት የቀረበው ይህ የኢቴቪ ዝግጅት ዋና አላማው «ተመልከቷት በመልካም ጤንነት ለይ ትገኛ ለች» የሚል መልዕክት ለማስተላለፍ ይመስላል:: ዓላማው ይህ ካልሆነ በስተቀር ከሌሎች የእስር ክፍሎች በተለየ ሁኔታ ብርቱካን የምትገኝበትን ክፍል ብቻ መርጦ ቁጭ ባለችበት ማሳየት ፋይዳው ምንድነው? የፕሮግራሙ ዓላማ የታራሚዎችን መልካም አያያዝ ለማስቃኘ ት ከሆነ ደግሞ እያንዳንዳቸው በርካታ የእስር ክፍሎች ያላቸው ከስድስት በላይ ዞኖች እያሉ ብርቱካን ያለችበትን ክፍል ብቻ መርጦ ማሳየት ስሜት አይሰጥም::

የወ/ሪት ብርቱካን እናት የሆኑት ወ/ሮ አልማዝ ልጃቸው መታመሟንና ተገቢውን ህክምና አለማግኘቷን ለተለያዩ ሚዲያዎች መግለጻቸውን ተከትሎ የሰሞኑ ዋነኛ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ ሰንብቷል። ጠ/ሚ መለስ በበኩላቸው ከሦስት ሣምንት በፊት ለውጭ የዜና ወኪሎች በሰጡት መግለጫ «የጤንነት ሁኔታዋ የተሟላ (perfect) ነው፣ በእርግጥ ባገኘሁት መረጃ መሰረት ክብደቷ ጨምሯል ያ ደግሞ ተገቢ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ ባለማድረጓ የተፈጠረ ሊሆን ይችላል» ነበር ያሉት።

ለመሆኑ ኢህአዴግ ብርቱካን አንድ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብላ የሚያሳይ ምስል በኢቲቪ መስኮት ስላቀረበልን በመልካም ጤንነት ላይ ለመሆኗ ማስረጃ ሊሆን ይችላል? ለመሆኑ ቀረፃው እሷ እያወቀች የተቀረጸ ነው? ከሆነስ በግዳጅ ወይስ በመልካም ፍቃደኝነቷ የተደረገ ነው? ከወላጅ እናቷ ባገኘሁት መረጃ መሰረት ለአመት በዓል የአበሻ ልብስ እንድትለብስ ጫና ተደርጎባት ሴራው ስለገባት ፍቃደኛ አልሆነችም። ታዲያ በስውር የተጠመደ ካሜራ ቁጭ ባለችበት ምስሏን አሳየንና እንዴት ልንቀበል እንችላለን? (በዚህ አጋጣሚ አንድ ታሪክ ላስታውሳችሁ የቅንጅት አመራሮች ከእስር ቤት በተፈቱበት ዕለት ኢቴቪ ሁነቱን ለመቅረፅ በማረሚያ ቤቱ የተገኘው ከማንም ቀድሞ ነበር። አመራሮቹ ግን ለመቀረፅ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገለፁ። የካሜራ ባለሙያዎቹ ግን በግቢው ላይ ባሉ ዛፎችና የጥበቃ ማማዎች ላይ ተደብቀው በመውጣት ቀረፃውን አከናወኑ በርካታ አንባቢያን የምታስታውሱትና የአመራሮቹ መፈታት ዜና በቴሌቭዥን ተደጋግሞ ሲቀርብ አብሮ ይቀርብ የነበረው ምስል በዚህ መልኩ የተቀረፀ ነው።)

በብርቱካን ዙሪያ ያሉ አወዛጋቢ ነገሮችን ለማጥራት መፍትሔው ምስሏን በቴሌቭዥን ማቅረብ አይደለም። በግሌ የብርቱካን ጤንነት በመልካም ሁኔታ ላይ መሆኑ አቋም ለመያዝ የምችለው ገብቼ የመጠየቅ መብት ሲኖረኝና ሁሉንም ነገር ከአንደበቷ መስማት ስችል ነው። ያኔ ደህና ነች ወይም አይደለችም የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ ያመቻል። በቴሌቭዥን ምስሏን ማቅረብ ግን ተራ የፖለቲካ ጨዋታ ካልሆነ በስተቀር ደህንነቷን አያረጋግጥልኝም። ለሂዩማን ራይትስዎችም ሆነ ለአሜሪካ ውጭ ጉዳይ መስሪያቤትም ምላሽ ሊሆን አይችልም። ቃሊቲ እንደሚገኝ እንደማንኛውም እስረኛ ማንም ሰው ገብቶ እንዲጠይቃት መፍቀድ ነው። ጠ/ሚ መለስ በተደጋጋሚ የብርቱካን እስር ሕግን ከማስከበርና ከሕግ የበላይነት ጋር በማያያዝ ደጋግመው መግለጻቸው ይታወሳል። እዚህ ላይ ግን አንድ አስቂኝ አንኳር ጉዳይ አለ። እሱም አንድ ታሣሪ በወዳጅ ዘመድ፣በጠበቃ፣ በሐይማኖት አባት ሊጎበኝ ይገባል የሚለውን ህገመንግስታዊ ድንጋጌ አለመከበሩ ብቻ ሳይሆን ይህ እንዲሆን ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ በማረሚያ ቤት (በአስፈጻሚ አካል) ተቀባይነት የማያገኝበት ህጋዊ አግባብ ምንድነው? የሚለው ነው። ፍርድ ቤቶች የሚሰጡት ትዕዛዝ አስፈፃሚ አካላት ሲጥማቸው የሚቀበሉት ሳይጥማቸው ሲቀር በግላጭ ውድቅ የሚያደርጉት ከሆነ በዚህች አገር እንዴት ስለህግ የበላይነት ሊወራ ይችላል? ስለ ሕግ ማክበርና ማስከበር ለመደስኮርስ ገዢዎቻችን እንዴት ሞራል ይኖራቸዋል። በዚህ ደረጃ ለፍርድ ቤት ውሳኔ እምቢተኛ የሚሆኑ የአስፈፃሚ ተቋማት ካሉስ በፍርድ ቤት ገለልተኝነት ውሃ የሚቋጥር መከራከሪያ እንዴት ሊቀርብ ይችላል። በፍርድ ቤቶች ለሚተማመኑ ዜጎችስ

(የራሱ አባላትን ጨምሮ)  ምን አይነት ስሜት ይፈጥራል። ለሴቶች መብት እቆማለሁ ሴቶችን ከጥቃት እከላከላለሁ የሚል መንግስት ወደደም ጠላም ይህን አለማድረጉ ከመወገዝ አያድነውም።

ሌላው አስገራሚ ነገር ደግሞ በዚሁ የቴሌቭዥን ፕሮግራም ላይ «ምስክርነት» ሲሰጡ የተመለከትናቸው የ«ፕሪዝን ፌሎውሺፕ» ኢትዮጵያ ዳይሬክተር ፓስተር ዳንኤል ገብረስላሴ የተናገሩት ንግግር ነው። ፓስተሩ ማረሚያ ቤቱ በሰብአዊ መብት አጠባበቅና በእስረኛ አያያዝ በአፍሪካ ተወዳዳሪ እንደሌለው ሲደሰኩሩ በተለይ ቃሊቲ እስር ቤትን የማያውቁና የኑሮ ውድነት ያስከራቸው ዜጎች «ምነው በታሰርኩ» ሊሉ ይችላሉ። ቃሊቲን አሳምረን ለምናውቃት ፤ለዚያውም በአንድ ክፍል ውስጥ 350 ሆነን ያለበቂ ኦክስጅን ከአእምሮ በሽተኞች ጋር ታስረን ሁለት አመት ላሳለፍንባት ሰዎች «እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሊቲ ከሪዞርት እና ሎጅ እኩል ነች» ብለው ቢደሰኩሩልን ከስላቅነት ያለፈ ምን ፋይዳ አለው? እንዲህ አይነት አለማዊ ስላቅ ደግሞ በሀይማኖት አባት አያምርም።

የቅንጅት  አመራሮችን ከእስር  በማስፈታቱ ሂደት ላይ በግንባር ቀደምትነት ከተሳተፉ የአገር ሽማግሌዎች መካከል አንዱ የሆኑት ፓስተር ዳንኤል አመራሮቹ የተፈቱበት ሂደት በሚገባ ያውቃሉ። ወ/ሪት ብርቱካን «ቃሌ» በሚል ርዕስ ያሰፈረችውን ሃሳብ ከዳግም እስራቱ ጋር በተያያዘ ያሉትን ሴራዎችና ክፍተቶች አሳምረው ያስተውሷቿል። ብርቱካን ታህሳስ 20/2001 ዓ.ም የእድሜ ልክ እስራቱ እንደፀናባት ተገልጾ በቁጥጥር ስር ስትውል ከፓስተር ዳንኤል ጋር ነበረች። ፕሮፌሰር መስፍንና ብርቱካን «እውነታውን ታውቁት የለም እንዴ? እናንተ አልነበራችሁም ወይ ሽማግሌዎቹ?» በማለት ነበር ፓስተር ዳንኤልን ያነጋገሩት - መፈትሄ አልነበረም እንጂ።

ፓስተሩም ሆኑ ሌሎች የአገር ሽማግሌዎቹ ቡድን አባላት «ብርቱካን ትክክል ነች» ወይም «አይደለችም» በሚለው ዙሪያ አስተያየት መስጠት አይፈልጉም። በተለይ ከቡድኑ አባልነታቸው ባሻገር «የኃይማኖት አባት» የሆኑት ፓስተር ዳንኤል  ባለፈው ሳምንት የኢቴቪ ትጉህ ልማታዊ ዘጋቢን አስተለው የቃሊቲ ማረሚያ ቤትን መልካም ገጽታ በማብሰር አላማ ላይ ተጠምደው ሰንብተዋል። ፓስተር ዳንኤል ይህን የማብሰር ሙሉ መብት እንዳላቸው አምናለሁ። ኢትዮጵያዊያን ከፓስተሩ መስማት የሚፈልጉት ምስክርነት ግን ይህ አይነቱ አለማዊ ምስክርነት አይመስለኝም። አዎ! ስለ ብርቱካን የእስር ቤት አያያዝ ብቻ ሳይሆን ለዳግም እስር የበቃችበት ነባራዊ እውነታም ሊመሰክሩልን ይገባል።

*ዳዊት ከበደ፣ የሳምንታዊው አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ማኔጂንግ ኤዲተር ነው  ለማንኛውም አስተያየት በኢሜይል አድራሻ davehadar@gmail.com ያገኙታል/